# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

6

★ የኢትዮጵያ አብዮት ከቺሊ የሚማረው

★ ዘመቻው በወዝ አደሩ ዓይን

★ የቦልሼቪክ ፓርቲ አጭር ታሪክ

★ የምርምር መሠረታዊ ስልቶችና ሁለቱ ተቃራኒ መልሶች

ሐምሌ ፲፰ - ፲፱፻፷፰ ዓ.ም.

## ርእሰ አንቀጽ ።

# « መከፋፈል » ወይስ ማጋለጥ ?

ማንኛውም አብዮታዊ እንቅስቃሴ ወዳጆች አሉት ። ጠላቶችም አሉት ። በመደባዊ አቀማመጣቸው ደግሞ የተነሣ መሀል ሰፋሪ በመሆን አብዮቱን በመደገፍና በመቃወም መሀል ለመሀል ተንጠልጥለው የሚዋልሉ ኃይሎች አሉ ። የአብዮታውያን ታክቲክ መነሻ የሚያደርገው ሳይንሳዊ በሆነ ዘዴ ኅብረተሰቡን ተንትኖ የአብዮቱን ወዳጆችና ጠላቶች በየወቅቱ ለይቶ ማወቅን ነው ። ከዚህም ጋር አብሮ የአብዮቱ ወዳጅ የተባሉትን በማንቃት ፤ በማደራጀትና በማስታጠቅ ላይ የአብዮቱ ጠላት ኃይሎችን ደግሞ በመበታተን ፤ በማዳከምና በመደምሰሱ ላይ ያተኩራል ። መሀል ሰፋሪ የሆኑ ኃይሎችን ደግሞ አረጋግቶና ለጥቅማቸው ዋስትና ሰጥቶ አብዮቱን እንዲደግፉ ያደርጋል ።

ይህንን የአብዮታዊ ትግል ስልት ዛሬ ተራማጁ ብቻ ሳይሆን የነቃውም አድሐሪ አምንበታለሁ ይላል ። ነገር ግን በአንድ አብዮት አንፃር ወዳጅና ጠላትን በመለየቱ ላይ የነቁ አድሀሪዎችና ተራማጆች እንደ አብዮትና ፀረ አብዮት ሁሉ የተለያዩ አቋሞች ይወስዳሉ ። በመሠረቱ የተራማጆቹ አቋም ከላይ የጠቀስነው ሲሆን ፤ የአድሐሪዎቹ ደግሞ የአብዮቱን ደጋፊዎች ሰፈር ለማዳከም ፤ ለመከፋፈልና ለመደምሰስ ፤ የአብዮቱን ጠላቶች ሰፈር ለማስተባበርና ለማጠናከር ይሞክራሉ ። መሀል ሰፋሪ የሆኑትን ኃይሎች ደግሞ አስቀይሞ ወደ ፀረ አብዮቱ ሰፈር የሚደባልቃቸው ርምጃዎች እንዲወሰዱ በተራማጅነት ስም ይወተውታሉ ።

ይህንን ፀረ አብዮት አድማቸውን ከሥራ ላይ ለማዋል የነቁ አድሐሪዎች ሁለት መሠረታዊ የሆነ የታወቁ ታክቲኮች አሏቸው ። አንደኛ የአብዮቱን ወዳጆች ሰፈር ለማዳከምና ለመከፋፈል ፤ ወዳጅ ተብሎ የሚቆጠረውን ኃይል እንደጊዜው ዋና ጠላት አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ የአብዮቱ ጠላት የሆነውን ኃይል እንደሌለ እንድንቆጥረውና እንድንዘነጋው ወይንም ደግሞ እስከነ አካቴው ወዳጅ አድርገን እንድናቅፈው ይጥራሉ ።

የመጀመሪያው የነቁ አድሃሪዎች ታክቲክ ከአብዮቱ ወዳጅ ኃይሎች ውስጥ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትን እንደኢትዮጵያ ሕዝቦች ዋና ጠላት ለማስቀጠር ሲፍጨረጨር የነበረውና የኢትዮጵያን ጭቁኖች ቀንደኛ ጠላቶች ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ችላ ብለን እሱው ላይ እንድንረባረብ ሲጋብዘን የነበረው የአናርኪስቶች ፤ የመሳፍንትና የኢምፔሪያሊስቶች አቋም ነበር ። ይህ በአብዮቱ ሰፈር ያለውን አሰላለፍ ለማዘበራረቅና ጭቁንን በጭቁን ላይ ለማስነሣት በየትም አገር ቢሆን ቀል ባሽ ኃይሎች የተጠቀሙበት የቅልበሳ ታክቲክ ነው ። ይህ ዘዴ በሀገራችንም የሳይንሳዊ ትንተና ካባ ደርቦ ስር ሊሰድ ሞክሮ የነበረው በከሀዲ አናርኪስቶች አማካኝነት ነበር ። በሀቀኛ ተራማጆች ቆራጥ ትግል ግን ይኸ ሴራ ስለተጋለጠ ዛሬ የአብዮቱ ሠፈር እየተሰበሰበና እየተጠናከረ በመጓዙ ከፀረ አብዮት ኃይሎች ጋር ለሚያደርገው ፍልሚያ ሠልፉን እያሳመረ በመሔድ ላይ ነው ።

ነገር ግን ይህ የኢትዮጵያ ተራማጆች ድል የነቁ አድሃሪዎችን ታክቲክ እንዲለውጡ አስገደዳቸው እንጂ ከአድኃሪ የትግል መድረክ እንዲሰናበቱ አላደረጋቸውም ። አሁን ደግሞ የሚቃጡት ሁሉን የአብዮቱ ወዳጅ አድርገው ለማቅረብ ነው ። «ወዳጅን ጠላት አድርጎ ማስመታት አልተቻለም ፤ እስቲ ደግሞ ጠላቱን ወዳጅ አድርገን እናቀርብውና ሰርጎ ይግባ» ይኸ ነው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአናርኪስቶችና የከሐዲ ንዑስ ከበርቴዎች መፈክር ሆኖ የቀረበው ።

ይህ ፀረ አብዮት ታክቲክ ገና በሚገባ አልተጋለጠም ። ከየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. ወዲህ በየጊዜውና በየደረጃው የመደቦች አሰላለፍ ተቀያይሯል ። በየካቲት ተራማጅ የነበረው ሁሉ ዛሬ ተራማጅ አይደለም ። ገና እንዳልካቸው ሲያልፍበት «አብዮታዊ» ሚናው ያከተመ ክፍል አለ ። የፊውዳሉ አገዛዝ ቁንጮ መስከረም ሁለት ላይ ሲወድቅ ፤ ሶሻሊዝም ሲታወጅ ፤ የመሬቱ ዓዋጅ ሲመጣ ፤ የቤቶች ዓዋጅ ሲጨመርበት ፤ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ወጥቶ የአብዮታቻን አቅጣጫ ቁልጭ ብሎ ሲተለም ፤ ሕዝቡ መንቃት ፤ መደራጀትና መታጠቅ አለበት ተብሎ የአድኃሪዎች ግብአተመሬት ነጋሪት ሲመታ ፤ ይኸ ሁሉ ተራ በተራ እያስደነገጠው ጠብ ጠብ እያለ አብዮቱን የከዳው ክፍል ስፍር ቁጥር የለውም ። ሌኒን እንዳለው እንዲህ ዓይነቱ የመደቦች መንሸራተት አንድ አብዮት በርግጥ አብዮት መሆኑን የሚያስመሰክርበት መለኪያ በመሆኑ እንደሰትበታለን እንጂ እንደናገጥበትም ። <u>ወደኋላ ጠብ ጠብ እያሉ የሚቀሩ ኃይሎች መኖራቸው ለአብዮታችን ወደፊት መራመድ ሕያው ምልክቱ ነው ።</u>

ስለሆነም አብዮታችን ወደፊት በገፋ ቁጥር ካለበት ደረጃ ወደፊት እንዲራመድ የመደቦችን አሰላለፍ እየደገሙ እየደጋገሙ መመልከትና ከድተው ወደኋላ የቀሩት ኃይሎች አሁንም ወዳጅ መስለው እንዳይደባለቁና እንዳያወናብዱ የትግሉንም ርምጃ እንዳይጐትቱት መጣር ያስፈልጋል ። አለበለዚያ «በዮሐንስ ጊዜ የደነቆረ በዮሐንስ አምላክ ሲል ይኖራል» እንደተባለው ይሆናል ። ይህንን የ«ወዳጅ መስሎ ጠላት» ሴራ ነቅተን ካልጠበቅን ፤ ጠብቀንም ካላጋለጥን ትላንት አብረውን የታገሉ ኃይሎች ዛሬ ጥቅማቸው ተነክቶ አብዮታዊነታቸው ሲያከትም ልብ ላንልና ለፀረ አብዮት ሴራቸው ደረታችንን ገልጠን ልንሰጥ እንችላለን ።

እርግጥ ይህ በየጊዜውና በየደረጃው የሚታደሰው የአሰላለፍ ትንተና የሚጠናወታቸው ኃይሎች አሉ ። ምክንያቱም የዚህ ትንተና ዓላማ የትላንትን ተራማጆች የዛሬ አድኃሪዎችን አበጥሮ ለማወቅና ለማጋለጥ መሆኑን ስለሚያውቁ ነው ። ስለሆነም እንዳይጋለጡ የሚፈሩ ኃይሎች ሁሉ እንደዚህ ያለው ትንተና ሲደረግ «የመከፋፈል ሴራ» ብለው ይቃወሙታል ። «መከፋፈል» ሳይሆን <u>ማጋለጥ</u> መሆኑን ስተውት ግን አይደለም ። የዋሆች ሳይሆኑ መሠሪዎች ናቸውና ።

አብዮቱን ክድቶ ወደ ሕዝብ ጠላቶች የተደባለቀው የነቃ አድሀሪ የመደቦች አሰላለፍ ለውጥ ጉዳይ ሲነሣ ጐራዴ ለመምዘዝ ይቃጣዋል ። «እንደዱሮው ሁሉም ተራማጅ ነው» ብሎ ክህደቱን ለመሸፈን ይፈልጋል ። ሰሞኑን አብዮቱን የካዱ ኃይሎች የተለቀቁበት የማወናበድ ዘመቻ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው ።

በዕድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ማጠቃለያ በዓል ሳቢያ ወጣቶች በአብዮታችን ውስጥ ስላላቸው ሚና ብዙ ውይይቶች ተደርገዋል ። በነዚህ ውይይቶች አማካኝነት ሁለት ጥርት ያሉ መሥመሮች ታይተዋል ። በአንድ በኩል የኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ያስከተለውን የአሰላለፍ ለውጥ በትክክል በማጤን አብዮታዊ ወጣቶችና ፀረ አብዮት ወጣቶች እያለ እየለየ ትንተና የሚያደርግ አቋም አለ ። በሌላ በኩል ግን እንዲሁ በደፈናው «ስለኢትዮጵያ ወጣቶች» እያወራ የአብዮታችን ሂደት ያመጣውን የመደቦች መንሸራተት የሚክድ ፤ ወጣቶችን በሙሉ ተራማጅ አስመስሎ ለማቅረብ የሚሞክር አድርባይና አድኃሪ አቋም አለ ። ይህ አቋም ከየካቲት በተለይም ትግላችንን የሚያግዙ አብዮታዊ ዓዋጆች ከወጡ ወዲህ ከኢትዮጵያ ተማሪዎች አንዱ ክንፍ ከወላጆቹ ጋር አብሮ ወደ ፀረ—አብዮቱ ሰፈር የመንጎዱንና አድሐሪ አቋም የመያዙን ሀቅ ስለሚክድ በአብዮታውያን ሠፈር ሰርገው እንዲገቡ ለነሱ የአድኃሪ ግልጋሎት መሞሸሪያ የአብዮታውያን ካባ ያለብሳቸዋል ። በአብዮታችን ላይ የሚደርሰውም ጥፋት የዚያኑ ያህል የከፋ ይሆናል ።

ይህ እንዳይሆን ተራማጅ ኃይሎች በየጊዜው ተስማሚ የሆነ ትንተና እያቀረቡና አብዮቱን የካዱትን ክፍሎች እየጠቆሙ በሰፊው ሕዝብ ፊት ማጋለጥ አለባቸው ። እንዲህ ዓይነቱ በየጊዜው የሚታደስ ትንተና ወዳጅ ተብለው ተደባልቀው የከዱትን ኃይሎች አጋልጦ አብዮቱን እንዳይቦረቡሩት ለማድረግ የሚሠነዘር የአብዮት ሰፈር የጽዳት ዘመቻ ነው ። በዚች የ«አብዮታዊት ኢትዮጵያ» እትም አንድ ወዝአደር እንዳለው ዛሬ በስመ ተማሪ ወይንም በስመ ዘማች ሁሉንም በጅምላ እንደተራማጅ የሕዝብ ወገን አድርጎ መውሰድን የመሰለ ከፍተኛ ስሕተት የለም ።

ስለሆነም በተራማጅ ወጣቶችና በአድኃሪ ወጣቶችና መሀከል ልዩነት አለ ማለት ወጣቶችን መከፋፈል አይደለም ። ይልቁንም ልዩነት አለ ብለን ብቻ ሳንቆም በወጣቱም መሀል የከረረ የመደብ ፍልሚያ መካሔድ አለበት ብለን ስመጠቆም አብዮታዊ ትግላችን ይበልጥ የጠራ መልክ እንዲይዝ ማገዝ የሀቀኛ አብዮታውያን የታሪክ ግዴታ መሆኑን እናውቃለን ። ይህን ማድረግ ያለውን የታሪክ ሀቅ አፍረጥርጦ በመናገር አድሐሪ ወጣቶችን ማጋለጥና የተራማጅ ወጣቶችን ሰፈር ማጠናከር ነው ። ይህ ትንተና ስለተደረገ «ክፍፍል መጣ» የሚሉ ኃይሎች በተራማጅነት ስም ሠርገን ገብተን ስንቦረቡር ተደረሰብን ብለው የሚያማርሩ ከሐዲዎች ብቻ ናቸው ።

አብዮታውያን ግን እንዲህ ዓይነቱን ትንተና እንኳን ልንፈራው ይቅርናጭራሽ የነፃነት ትግላችን የማይነጠል አካል አድርገን እንቀጥረዋለን ። በረዥሙ የአብዮት ጉዞ የትኛው መደብ የትኛው ፊርማታ ላይ ሊሰናበት እንደሚችልና እንደተሰናበተም አፍረጥርጦ ማሳየት ለትግላችን የሕይወት እስትንፋሱ ነው ። ይህንን ማድረግ የማይደፈር ታጋይ በአድርባይነትና በእወደድባይነት መርዝ የተበከለ የጭቁን ሕዝቦች ጠላት እንጂ የትግላቸው አጋዥና ግንባር ቀደም ተሳታፊ ሊሆን አይችልም ።